# ተልባ ቢንጫጫ

የሳጥናኤልን ሰራዊት
በአንድነት ቢያሰለፉት
አንድ መልዓክ አይመክት
እንደ ተቃዋሚዎች ቢሆንማ
ማን ይተርፍ ነበር? እኮ ማ?
ኢዴፓቅ አሉን ሲጀምሩ
አብረው አንድ ቀን ላያድሩ
አማራጭ አሉ እንደገና
አንድ ዓመት መች ቆዩና
ተጣልተው ሲለያዩ ዓይን ላፈር
ተመልሰው መገናኘታቸውም ባይቀር።

ሕብረት ብለው መጡ ሰነባብተው
ባይቀርም ቅሉ ጉንተላቸው
ሳይውል ሳያድር ህብረቱ
ወጡ እንጅ ከአንድነቱ።

ትልቅ ዲያብሎስ ፈጠሩ
ቅንጅት ብለው ቀጠሉ
የዲያብሎስ መጨረሻው ጥፋት
አስከተለ ታላቅ እልቂት
የወገንን ሞት
የሃገር አንጡራን ውድመት።

ጉሮሮዬ እስኪነቃ
ብታደርቀኝም ልብ አውቃ
ብታረግዝም ሚስትህ
የጠብ ደቦ አማረኝ ብትልህ
የለህ ቁም ነገር አትሰጣት
እንደ አንድነታችሁ ሂደት
የጠብ ደቦ ከሆነው ህብረት
አትለይምና በድርጊት
የእርጉዝ ሚስትህ ሓምሮት
የትም አያደርሳት።

እናንተና እናንተን መሳዮች
ሰላም የማይጥማችሁ ወገኖች
ብትተባሩም እልፍ ጊዜ
በያዛችሁ አባዜ
አላማችሁ ፀረ-ሰላም ነውና
እድገት አይታየውምና
ከምላሴ ጸጉር
ትወስዳለህ ዘወትር
የአንተ ድል ቢበሰር።

የጀመርከውን ሙግት
ህዝብን በህዝብ ላይ ማነሳሳት
ማበሩን የሚሰራን ሰው ለማወክ
ሃገርን በሚጎዳ መልክ
አይጋ ፎረምን መነካካት
መቀለዱን በሃገር ሰላም አንድነት
አቁመው እወቅበት
ተማር ከሰላም ኀይሎች ቅንነት።

እልሃለሁ ዳግማዊ ወዲ ዳዊት
ቀቢፀ-ተሰፋ ወልደ-ጥፋት
የተቃዋሚወች ሩጫ
ሁሌም ያው ተልባ ቢንጫጫ
አያልፍምና ካንድ ሙቀጫ።

ደሳለኝ በርሄ desberhe@gmail.com